# የሊድ ቅብን ከቤትዎ መቀነስ ይፈልጋሉ

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

ከቤታቸው ውስጥ የሊድ መሰረት ያለውን ቅብ ለመተካት፣ ነዋሪዎች ከእኛ —የዲሲ መንግስት— የገንዘብ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። የሊድ መሰረት ላላቸው የቅብ ጥገናዎች፣ **እስከ $11,000** የሚሆን እርዳታ መቀበል ይችላሉ። ለፕሮጀክቶቹ ክፍያ ለመክፈልና በቤትዎ ያለውን ስራ የሚጨርስ ጠጋኝ ሰው ለማግኘት፣ በአካባቢ ካለ ለትርፍ ከማይሰራ ድርጅት ጋር አብረን እንሰራለን።

ይህ ፕሮግራም የሊድ ቅነሳ ፕሮግራም ይባላል እንዲሁም በሃይልና አካባቢ ዲፓርትመንት ቀርቧል።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ **ሁሉ**መግለጫዎች እውነት ከሆኑ፣ ብቁ ነዎት፡

- በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ።
- ከእርስዎ ጋር የሚኖር 6 አመትና ከዚያ በታች ይሆን ህጻን ወይም ቢያንስ ሶስት ሰአት በቀን፣ ሁለት ቀን በሳምንት፣ ወይም 60 ሰአታት በአመት በቤትዎ የሚያሳልፍ ከሆነ፣ ወይም ነፍሰ ጡር ሰው ከእርስዎ ጋር አብሮ የሚኖር ከሆነ።
- ከ 1978 በፊት በተሰራ ህንጻ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ።
- የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ —ግብርን ከመክፈልዎ በፊት ያለው የእርስዎ ገቢ— በቤተሰብዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ነው። ገቢዎን ለማስላት፣ አብረው ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን አዋቂ ሰዎች ገንዘብ ይደምሩ፡፡ ከዚያ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉትን ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ደህንነት፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያዎች የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ። ለማወቅ ከስር ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $70,500 |
| 2 | $80,650 |
| 3 | $90,700 |
| 4 | $100,800 |
| 5 | $108,850 |
| 6 | $116,950 |
| 7 | $125,000 |

ለዚህ ፕሮግራም ለማመልከት የቤት ባለቤት መሆን አይጠበቅብዎትም።

# ያመልክቱ።

1. የቤተሰብ ገቢ ማረጋገጫን ይሰብስቡ፣ ይህም የቅርብ ጊዜ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም ለእርስዎና ለቤተሰብዎ አባላት የታክስ ተመላሾችን ያጠቃልላል። የሚያስፈልጉዎት ለእርስዎ ሁኔታ የሚሆኑ ሰነዶችን ብቻ ነው።
2. ማመልከቻውን ይሙሉ፣ የቤተሰብዎን ገቢ ማረጋገጫ ያያይዙ እንዲሁም በኢሜይል ወደ LaWanda.Jones@dc.gov ይላኩ ወይም ከስር በተቀመጠው አድራሻ ይላኩ። ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ይኖርብዎታል። እባክዎን ዋናውን ሰነዶች አይላኩ።

   Department of Energy & Environment, Energy Administration
   Attn: LaWanda Jones
   1200 First Street NE, 5th Floor
   Washington, DC 20002

በማንኛውም ሰዓት ማመልከት ይችላሉ። ከማመልከት ይልቅ ወደ ፕሮግራሙ ሊላኩ ይችላሉ። ከስድስት አመት በታች የሆነ ህጻን ልጅ በደሙ ውስጥ ከፍ ያለ የሊድ መጠን ካለው፣ የልጁ ዶክተሩ እኛን—የዲሲ መንግስት— እርዳታ እንድናደርግ ያነጋግረን (ቢሆንም ችግሩን በፍጥነት መፍትሄ ለመስጠት በቀጥታ

እንዲያመለክቱ አሁንም እናበረታታዎታለን!)። በአካባቢው ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት፣ በሌላ የዲሲ መንግስት ኤጀንሲ፣ በጠበቃ ወይም በሌላ ሰው ተልከው ሊሆን ይችላል።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. በማመልከቻዎ በአንድ ቀን ውስጥ፣ እኛ—የዲሲ መንግስት— ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዳገኘ ለማሳወቅ እንደውልልዎታለን እንዲሁም ክፍያ ለመክፈልና ለስራው ለማመቻቸት፣ በአካባቢው ያለን ትርፋማ ያልሆነ ድርጅት እንመርጣለን።
2. በአካባቢው ያለ ትርፋማ ያልሆነ ድርጅት ቤትዎን የሊድ ምርመራ ለመመርመር ጥገና ለሚያደርግው ሰው ያዘጋጅለታል። በቤትዎ ውስጥ የሊድ መሰረት ያለውን ቅብ ለማስወገድ እና ለማደስ፣ የወጪውን ግምት ምን ያህል እንደሆነ እነሱ ያቀርቡልናል። በፍተሻቸው ጊዜ ማንኛውም ሌላ የሊድ ምንጮችን ካገኙ፣ እኛ እናሳውቅዎታለን እንዲሁም ያንን ለመፍታት ከእርስዎ ጋር አብረን እንሰራለን።
3. ጥገና የሚያደርገው ሰው የሊድ መሰረት ያለውን ቅብ ያስወግደዋል ወይም ይጠግነዋል፣ ጥገናዎቹ በትክክል እንደተደረጉ ለማረጋገጥ ሙከራ ያደርጋል እንዲሁም ቤትዎን እንደገና ለሊድ ይፈትሻል።
4. ቤትዎ ከሊድ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው! እርስዎ ወይም የእርስዎ አከራይ ቤትዎን የሊድ ቁጥጥር ሊያደርግ እና ደህንነቱን ሊጠብቅ ይስማማል።

ለጥገናዎቹ ፈቃድ ካላገኙ፣ እርዳታ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች ፕሮግራሞችን እናሳውቅዎታለን።

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች የሊድ መሰረት ያላቸውን ቅቦች ይተካሉ?

አይ፣ ለጥገናዎች የሚሰጠው ገንዘብ መጀመሪያ በመጣ፣ መጀመሪያ በተስተናገደ መሰረት ላይ ያለ ነው። ይህ ፕሮግራም የተከፈተው በ 2020 ነው ስለዚህ ምን ያህል ነዋሪዎች እንደሚያመለክቱ፣ ወይ ገንዘብ እንደቀበሉ እርግጠኞች አይደለንም።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

አንዳንድ ግዜ፣ ስራ ተቋራጩ ጥገናዎቹን ለማድረግ እርስዎ ሌላ ቦታ እንዲሆኑለት ሊፈልግ ይችላል። እኛ—የዲሲ መንግስት— እንደየጉዳዩ ሁኔታ የማዛወርን ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ ልናቀርብ እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ እርስዎ ወይም የእርስዎ አከራይ ለእርስዎ የመዛወር ወጪዎች ሃላፊነቱን ሊወስድ ይችላል።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎ የሊድ ቅነሳ ቡድንን በ(202) 236-2657 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am

እስከ 5 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ያግኙ። ወይም በ LaWanda.Jones@dc.gov ላይ “Lead Reduction Program” በሚል ርዕሰ መስመር ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

**የቤቴን ደህንነት ለመጠበቅ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
በእኛ የቤት ደህንነት እና የሊድ መከላከል ገጾች ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**
**ጥገናዎቹን ለቤቴ አግኝቻለሁ እንዲሁም እራሴ ከመኖር ይልቅ ለማከራየት ወስኛለሁ መከተል ያሉብኝ ማንኛውም ልዩ መስፈርቶች አሉ?**
አዎ። ጥገናዎቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ላሉት ሶስት አመታት፣ ቤትዎን ሲያስተዋውቁና ሲያከራዩ ስድስት አመትና ከዚያ በታች ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ወይም ለነፍሰ ጡር ሴቶች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ቤትዎን የሊድ ቁጥጥር ማድረግዎንና ደህንነቱን መጠበቅዎን መቀጠል አለብዎት።

**ጥገናዎቹን ለማግኘት መክፈል ያለብኝ ማንኛውም ነገር አለ?**
እኛ—የዲሲ መንግስት— የመጀመሪያ ፍተሻውን፣ ጥገናዎቹን፣ ምርመራዎቹን እንዲሁም የመጨረሻ ፍተሻውን በማካተት የሂደቱን አጠቃላይ ወጪዎች እንሸፍናለን። ጥጋናዎቹ ሲከናወኑ ማዛወር ማስፈለገዎ፣እንደየጉዳዩ ሁኔታ የማዛወርን ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ ልናቀርብ እንችላለን። የሊድ ቁጥጥር ለማድረግና ወደፊት ቤቱን ከሊድ ነጻ አድርገው እንደሚጠብቁ መስማማት አለብዎት፤ እንዲሁም ያንን ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን እርስዎ ሃላፊነቱን ይወስዳሉ።

**ስራውን የሚየጠናቅቀው ማን ነው?**
ለጥገናዎቹ ዝግጅት የሚያደርገው እና ክፍያዎቹን የሚፈጽመውን በአካባቢ ያለ ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት እንመድባለን። አግባብነት ያለው የምስክር ወረቀቶች ባሉትና ፈቃድ በተሰጠው የጥገና ግለሰብ ጥገናዎቹ ይጠናቀቃሉ።

**የጥገና ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?**
በቤትዎ መጠን እና ምን ያህል ስራ መሰራት እንደሚያስፈልግ ላይ ተመስርቶ፣ ጥገናዎች ከ 1-10 የስራ ቀናት ይፈጃሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጥገናዎቹ ረጅም ጊዜ ሊፈጁ ይችላሉ።

**ይህ ፕሮግራም ልጄ ለሊድ መጋለጥ አለመጋለጡን ለማወቅ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል?**
አይ፣ ልጅዎ ለሊድ መጋለጡን ፕሮግራሙ አይመረምርም። በህጉ መሰረት፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚኖሩ ሁሉም ልጆች ከ 6-14 ወራት እና ከ 22-26 ወራት እድሜ ላይ የሊድ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ማስታወስ የሚቻልበት ቀላሉ መንገድ፡ እያንዳንዱን ልጅ መርምሩ፣ ሁለት ጊዜ በሁለት። በተጨማሪም፣ ስድስት አመትና ከዚያ በታች የሆኑ ጥገናዎች በተደረገበት በቤት ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ህጻናት የሊድ መጋለጥ ምርመራን እንዲያደርጉ እንጠይቃለን። ለሊድ ፍተሻ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የህጻናት ሀኪምዎን ወይም የዲስትሪክቱን የህጻናት የሊድ መመረዝ የመከላከል ፕሮግራም በ 202-535-2600 ላይ ያነጋግሩ።

**ይህ ፕሮግራም ከፍ ያለ የደም ውስጥ ሊድ መጠን ያላቸውን ህጻናት ለያዙ ቤተሰቦች ቅድሚያ ይሰጣል?**
አዎ፣ ከፍ ያለ የደም ውስጥ ሊድ መጠን ያላቸውን ህጻናት ለያዙ ቤተሰቦች ቅድሚያ እንሰጣለን።

**ቤተሰቤ ምንም አይነት ገቢ የለውም። ያንን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?**
ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር **ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሰነድ ማስገባት** ይችላሉ፡

- በውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠ የገቢ መግለጫ፣
- Department of Employment Services (DOES፣ በቅጥር አገልግሎቶች ክፍል) ድረ ገጽ “ቀሪ ሂሳብዎ” ዜሮ እንደሆነ የሚያሳይ የእርስዎ “ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መገለጫ” ቅጽበታዊ ገጽ እይታ(ምሳሌውን ይመልከቱ)፣
- ከቀድሞ አሠሪዎ የተጻፈና ከአሁን በኋላ እዛ እንደማይሠሩ የሚገልጽ ደብዳቤ (ከስራ ከለቀቁ ግን እስካሁን ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን በ DOES እያገኙ ካልሆነ)፣ ***ወይም***
- ከ District of Columbia Housing Authority (DCHA፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን) የመጣው ደብዳቤ የሚገልጸው ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ እንደሌለው ነው።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*